# መሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ለምርት አገልግሎት ጠቅላላ ከምንጠቀምበት 85,000 ሜትሪክ ቶን የታጠበ 105,000 ሜትሪክ ቶን ያልታጠበ የሀገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል አቅራቢዎችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል

የተለቀቀበት ቀን: ሰሉስ ነሓሰ 28, 2016 (ከ 1 ዓመት)
መዝግያ ቀን: ሰሉስ መስከረም 7, 2017 08:00 ከሰአት (ተዘጋ)
የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:1,000,000
ቦታ:መቐለ
የጨረታ ደኩመንት ዋጋ:1000
ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: ሰሉስ መስከረም 7, 2017 08:30 ከሰአት
ምድብ: ጠቅላላ ስራሕቲ ኣገልግሎት/ ኤሌክትሮ-መካኒክስ ኣቁሑትን ግልጋሎትን/ ኬሚካልን ሪኤጀንት/

ለምርት አገልግሎት የሚውል ውስጥ ድንጋይ ከሰል አወዳድሮ ለመግዛት የወጣ ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

መሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ለምርት አገልግሎት ጠቅላላ ከምንጠቀምበት 85,000 ሜትሪክ ቶን የታጠበ 105,000 ሜትሪክ ቶን ያልታጠበ የሀገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል አቅራቢዎችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል። በዚህ መሰረት የጨረታ ሰነዱን መሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ አዲስ አበባ ስታድ ም ወጋገን ህንፃ 3ኛ ፎቅ በሚገኘው ቢሮአችን ወይም መቐለ ዋና መስራቤት በአካል በመገኘት መግዛት የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን።

በዚህ መሰረት ተጫራቾች፣

- በጨረታው የሚሳተፉ ድርጅቶች የከሰል ድንጋይ በማምረት በዘርፉ የተሰማሩ መሆናቸው የሚገልፅ ህጋዊ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ መሆናቸው፣ የመዐድን ፈቃድና የመሬት ይዞታ ሰርተፊኬት የሚግልጽ ማስረጃ ከጨረታ ሰነዳቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። የታጠበ የድንጋይ ከሰል ለሚያቀርቡ ደግሞ የድንጋይ ከሰል ማጠቢያ ፋብሪካ ባለቤት መሆናቸውና የስራ ፈቃድ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።
- ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ብር 1,000,000 (አንድ ሚልዮን ብር) በመሰቦ ስሚንቶ ፋብሪካ ሃ/የተ/የግ/ማ ስም የተዘጋጀ በባንክ የተረጋገጠ ቼክ (CPO) ወይም ባንክ ጋራንቲ ለብቻው በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።
- ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ከላይ በተራ ቁጥር 2 ከተጠቀሱት ማስረጃዎች ጋር በማያያዝ የድርጅታቸውን አርማና ማህተም ያለው ደብዳቤ በመፃፍ ለጨረታ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
- ተጫራቾች ከዚህ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ጋር አብሮ ከተገለፀው ዝርዝር መግለጫ መሰረት ያቀርቡትን የሃገር ውስጥ ድንጋይ ከሰል (የታጠበ/ያልታጠበ በጨረታው ቀን ወይም ከዛ በፊት በራሳቸው ወጪ ለምርመራ ናሙና (ሳምፕል) ቢያንስ 10 ኪ.ግ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። (ናሙናው የሚቀርበው መቀሌ በሚገኘው ዋና ፋብሪካ ይሆናል)
- ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያቸውና በተራ ቁጥር 2 እና 3 ላይ የተጠቀሱት ሰነዶችና በተራ ቁጥር 4 የተጠቀሰውን ናሙና (ሳምፕል) እስከ መስከረም 07/ 2017 ከሰዓት በኋላ 8:00 ሰዓት ድረስ በታሸገ ኤንቨሎፕ የጨረታ ሰነዳቸው መቀሌ በሚገኘው የፋብሪካው ዋና መስሪያ ቤት 3ኛ ፎቅ ቁጥር 15 ስለሚገኝ የግዥና አቅርቦት ቢሮ ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።
- ጨረታው በእለቱ መስከረም 07/ 2017 ከሰዓት በኋላ 8:30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል።
- ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ 1000 (አንድ ሺህ ብር) በመክፈል መግዛት የምትችሉ መሆኑ እንገልፃለን
- ፋብሪካው ጨረታው በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

ለተጨማሪ ማብራሪያ በስልክ ቁጥር

+251 34 440 5806/+251 912 502 596/

+251 914 729 516 ወይም procurementmessebocement2020@gmail.com መጠቀም ይቻላል።

መሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ኃ.የተ.የግ/ማህበር